# <u>ሲሰነጠቅ ጠፈር ሲተረተር ሰማይ</u>

ሲሰነጠቅ ጠፈር ሲተረተር ሰማይ፣
ሲፎክር ሲያጓራ ሲያቅራራ ከአናት ላይ፣
ሲነጠቅ ሲለጠጥ ሲናኝ በሰማያት፣
ነጎድጓድ ሲያጓራ አዋስኖ ቀላያት፣
ብራቅ ተወላግዶ ሲባርቅ በፍጥነት፣
ምድር ስትደምቅ ለአንድ አፍታ ከመቅጽበት።

ሰማያት ሲለብሱ የወርቅ ግምጃ ምንጣፍ ፣
ሲገለጥ ሲከፈት የገሐነም ደጃፍ።

ሲሽቆጠቆጥ ጠፈር በብርሃነ ጮራ፣
ኋፍረቷ ሲገለጥ ሳታፍር ሳትፈራ።

ለመቅጽበት ሲታይ እሳት ቶን ተፈልጦ፣
ፍጡር በመደነቅ ሲያንጋጥጥ ደንግጦ ።

መለኮታዊው ድምጽ ሲደመጥ ከጥልቁ፣
ሲከሰት ሲከፈት ሰማያት ከሩቁ፣
ሲከፈት ሲከሰት መለኮተ ድብቁ ።

ፍጡር ተቀስፎ በነጎድጓድ ሲዋጥ፣
ብልጭታ ሲገዝፍ ሲያርድ ሲያንቀጠቅጥ።

ምድር እርጭ ሲል ነጎድጓድ ሲገዝፍ፣
ሲሽማቀቅ ሰማይ ፍጡር ሲንዘፈዘፍ ።

ሲወጋ ሲያቆስል በብራቁ ሾትል፣
መደበቂያ ዋሻ ጊዜ እልም ሲል።

ብርሃንም ሲነግስ ነጎድጋድን ለብሶ፣
ሲደመጥ ከሩቁ አስደንጋጩ ለቅሶ።

የሰማያት ማሳ በብርሃን ሲታረስ፣
ምድር ስትሸሞን ተላብሳ ኮሳኮስ።

ብርሃን እሳት ሲሆን ሲተበት በአዙሪት፣
ፍቅር ቁጣ ሲሆን ሲሳሳም ከመሬት፣
የወርቅ ጥና እሳት ለባሽ የመለኮት፣
ሲገለጥ ሲከሰት የዘለላለም እሳት።

ዝርግፍ ወርቅ ሆኖ የእሳት ሰረገላ፣

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ምድር ውቅያኖስ ሰማዩን ሲሞላ፣
ቀስፎ አስሮ ሲጥል ቋጠሮው ሳያላላ፣
ጥሩር በ ጸዳሉ  ፍኖት ሆኖ ጥላ ።

ሲያመነጭ ፍላጻ ብርሃን ፍንጥቅጣቂ፣
ሲፎክር ሲያቅራራ የእሳትጦር ሰባቂ፣
ሲያቅራራ ሲፎክር እሳት ጦር ስንጣቂ፣
ሲጎሰም ሰማያት የድምጽ ፍልቃቂ።

ልሳንም ሲዘጋ ጽልመት ሲሆን ፍርሃት፣
አልቦ ሲሆን ዜማ የዲያቆን ካህናት፣
ሲተካ በእግዚኢነ ሲማተብ በጸሎት፣
ነቁጥ  ተለውጦ ሆኖ ሲቀር ጭረት፣

በምሁር ተመስሎ ያደረው ሽምግሎ፣
ሲማገድ ሲቃጠል በእሳት ጦር አሎሎ፣

የቋያ እሳት ሰደድ የትግሉ ወላፈን፣
የነበልባል ጉራጅ ቀንዲል እሳት ሲሆን፣
ተቀይዶ ሲያዝ ከአንቀልባ እስከ ከፈን።

ቡላድ ነድ ሲሆን ዘረኛ ሲጠፈር፣
ሐሰት ስትነጥፍ በኢትዮጵያ ምድር፣
መገለጫ ሲሆን የነጻነት ክብር፣
መጥበሻ  ማንጠሪያ ለኢትዮጵያዊ ፍቅር።

መቀጣጫ ሲሆን ለመርገመ ስጋ፣
ዝንተ ዓለም ለመኖር ያሰበው ሳይሰጋ።

የስጋዬ ክፋይ የሆንከው ወገኔ፣
ፈጥኖ ለመረዳት ትሻላለህ ከኔ፣
እኔነትህ ሞልቶ በአባቶችህ ወኔ፣
የነፃነት ትግሌን ጻፈው በጠመኔ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com